የረቡዕ ጥር 11 1779ዓ.ም ( የጃንዋሪ 19 20050)

## የፍኖተ ዴሞክራሲ ሐተታ

### ርሀብ በልመና አይወገድም

በ1984 ዓም የተከሰተውን የኢትዮጵያን ረሀብ አስመልክቶ ማርክስ በርግ የተሰኘ የቢቢሲ ቴሌቪዥን ጋዜጠኛ ሰፊ የቴሊቪዥን ዘገባ በማቅረብ የዓለምን ኅብረተሰብ እንዳሳዘነውና ለረሀብተኞችም አስቸኳይ ርዳታ እንዲጎርፍ ምክንያት እንደሆነ የቅርብ ትዝታ ነበር።ያ አሰቃቂ ትዝታ ለኛ ኢትዮጵያውያንን ብቻ ሳይሆን፥ በመላው ዓለም ኅብረተስብ ጭምር የማይረሳ ጠባሳ ጥሎ ሄዷል። ከሀያ ዓመታት በኋላ ይኸው ጋዜጠኛ፤ ዛሬም ረሀብ በኢትዮጵያ በበርካታ ሚሊዮን የሚቆጠሩትን ዜጎች እንደቀጠል እያረገፈ መሆኑን በመግለጽ ሰፊ ዘገባ አቅርቧል። የዚህ ዘገባ ይፋ መሆን ከአስቆጣቸው የወያኔ ባለሥልጣኖች መካካል፥ በእንግሊዝ ሀገር የመለስ ዜናዊ አምባሳደር ፍስሐ አዱኛ ግንባር ቀደሙን ቦታ ይዟል። ፍስሐ አዱኛ የረሀቡን ዜና የሚገልጸውን ጽሁፍ ያቀረበውን ጋዜጠኛ በመዝለፍ፤ ረሀቡ በቁጥጥር ስር እንደዋል ለማስተባበል ሞክሯል። ከዚህም አልፎ-ተርፎ፥ ወደፊት ወደ ኢትዮጵያ በሚሄዱ ሀገር ጎብኝዎችና ጋዜጠኞች ላይ ከፍተኛ ቁጥጥርና ማዕቀብ እንደሚደረግ ለማስፈራራት ጥሯል። ልክ ከእርሱ በፊት እንደነበሩት መንግሥታት፥ መለስም ርሀቡን አስመልክቶ ማነኛውም ነገር በቁጥጥር ስር እንደሆነ ለማጭበርበር እየሞከረ ነው። " አምባሳደር ማለት በተላከበት ሀገር ሄዶ የሚዋሽ ነው" የሚለውን የዲፕሎማቲክ ይትባህል ባንስተውም፥ የፍሰሐ አዱኛ ውሸት ግን፥" የሌባ ዓይን ደረቅ፥ መልሶ ልብ ያድርቅ" ከመሆን አያልፍም። መላው ዓለም ያወቀውን ሀቅና የኢትዮጵያ መለያ የሆነውን ረሀብ፥ ብሎም፥ ከ 10-እስከ 15 ሚሊዮን የሚሆነው ዜጋችን በረሀብ መጠቃቱን አላፊ አግዳሚው እየተገነዘበው፥ የወያኔው አምባሳደር ባህር ማዶ ሆኖ ለማስተባበል መሞከሩ ከድንቁርና በስተቀር ሌላ ትርጉም የሚሰጠው አይሆንም። ይህ የወያኔው አምባሳደር፥ በዛሬይቱ ኢትዮጵያ፥ በጠኔ ምክንያት፥ በበርካታ ሚሊዮኖች የሚቆጠሩ ዜጎች እየተመተሩ መሆናቸውን ሊክድ ቢከጅልም፥ የኢትዮጵያ ረሀብ፥ ጋዜጠኞች የሚፈጥሩት አሉባልታ ሳይሆን ሀቅን የተጎናፀፈ፥ ዕውነትን የተመረኮዘ ዕውነታ ነው። የመለስ አገዛዝ ራሱ በተጀመረው የፈረንጅ ዓመት 7 ሚሊዮን ኢትዮጵያውያን የምግብ እርዳታ ያሻቸዋል ሲል የልመና አቁማዳውን ለዓለም አሳይቷል።

የአምባሳደሩን ዓይን ያወጣ ማስተባበል የሰሙት፥ ም/ር ማርቲ አስተሪ፥ የአካባቢው የተባበሩት መንግሥታት ተወካይ፥ የሚከተለውን መግለጫ ሰጥተዋል። እንጠቅሳለን " በዕርሻ ይዞታዋ ላይ ከፍተኛ የሆነ መሠረታዊ ለውጥ ካላደረገች፥ ኢትዮጵያ ከድኅነትና ከረሀብ ትገላገላለች ማለት ዘበት ነው። ሀገሪቱ ከድህነትና ከጥገኝነት ልትወጣ ጭራሽ አትችልም። ይህም ምክር

በዓለም ባንክና በሌሎች ለጋሽ ሀገሮች አማካኝነት ተደጋግሞ ተገልጾላታል::”
የጥቅሱ መጨረሻ:: በሚሊዮን የሚቆጠሩ የኢትዮጵያ ገበሬዎች የበሬ ግንባር በምታህል ቁራሽ መሬት ላይ እያረሱ፥ ኢትዮጵያ ሕዝቧን ለመመገብ አትችልም:: መለስ ዜናዊ ግን ይህን ሀቅ አልቀበል ብሎ ብዙሀኑ አርሶ አደር የመሬት ባለቤትነትን አይፈልግም፤በሰላም ተደስቶ እያረሰ ነው ከማለቱ ሌላ ከሁለት ዓመት በኋላ ኢትዮጵያ ራሷን ሙሉ በሙሉ ትመግባለችም ብሎ ተፈጥሚል:: በቀን ሶስቴ ትባላችሁ በወያኔ አገዛዝ ያለን ዓይነት ተስፋ መሆኑ ነው:: በወያኔ ሞልቷል የወሬ ጠኔ ማለት እንችላለን::

በአሁን ጊዜ ኢትዮጵያ ወስጥ ያለው የግብርና ፖሊሲ የኢትዮጵያን ገበሬ የመንግሥት ጪሰኛ እንዲሆን ከማድረግ አልፎ፥ ገበሬውን ተግቶ እንዲሰራ የሚያደርግ ማበረታቻ ስለማይሰጠው፥ የግብርና ልማት ከማደግ ይልቅ ሁሉ ጊዜ እየቆረቆዘ እንደሚሄድና፥ ይህም ከአፈር መታጠብና መሸርሸር ጋር ተደምሮ የገበሬውን ህይወት ከ20 ዓመት በፊት ከነበረበት ሁኔታ የባሰ አስከፊ እንዳደረገው፥ ም/ር ማርቲ አታሪ ዘርዝረዋል:: መሠረታዊው ችግር፥ ወያኔ እየተከተለ ያለው የግብርና ፖሊሲ መሆኑን ገልፀው፥ የወያኔ ማርክሳዊ-ስታሊናዊ የመሬት ባለቤትነት ፖሊሲና የተሳሳተ የሰፈራ ፕሮግራም፥ ችግሩን ከማባባስ ያለፈ ያመጣው ፍይዳ እንደሌለ ገልፀዋል:: በተጨማሪም፥ ሀገሪቱ ካላት የዓመት ገቢ ወደ 6 ከመቶ የሚጠጋውን የምታውለው ለወታደራዊ ወጭ በመሆኑ ለግብርና ልማት ሊውል የሚገባው ሀብትና ባጀት ያለ አግባብ እየባከነ መሆኑንና ይህም የወያኔ የቅደም ተከተል ተግባር የተዛባ መሆኑን ያመለክታል:: ወትሮውንም ቢሆን መለስና ግብረአበሮቹ ለኢትዮጵያ ልማትና ዕድገት የመጡ ስለአልሆኑ፥ ይህ መሆኑ አያስደንቅም:: መለስ ግን ይህን ሁሉ ሀቅ ክዶ አርሶ አደሩ የሚፈልገው በእርሻው ላይ በሰላም ማረሱ እንዲረጋገጥለት ብቻ ነው፤ይህንንም አረጋግጠናል ብሎ በሀሰት ይመፃደቃል::

የዓለም አቀፍ ባለሙያዎች፥ ተቋማትና የኢትዮጵያ ተቃዋሚ ኃይሎች፥ የኢትዮጵያ የመሬትና የግብርና ፖሊሲ መሻሻል እንዳለበት የተደጋገመ ማሳሰቢያና መግለጫ ቢያቀርቡም፥ የመለስ ዜናዊ ቡድን ከመጤፍ ሊቆጥረው አልቻለም:: ሰለሆነም፥ ለረሃብ ከሀገሪቱ መወገድና ለሁለገብ የልማት ዕድገት እንቅፋት የሆነው የመለስ ቡድን ፥ ሥልጣን ላይ እስካለ ድረስ ወደከፋ ደረጃ መድረሳቸውን የማይቀር መሆኑን ኢትዮጵያውያን ብቻ ሳይሆኑ፥ የመላው ዓለም ኅብረትሰብም ተገንዝቦታል::

የኢትዮጵያን ሁለንተናዊ ችግሮች አስምልክቶ፥ ከሀገር ውስጥም ይሁን ከመላው ዓለም፥ አንድ ዓይነት ድምጻሜ ቢደረስም፥ ድምጻሜው ከግንዛቤ አልፎ ለውጥ ለማምጣትና ውሳኔ ለማድረግ አልተቻለም:: የሀገሪቱ መሠረታዊ ችግሮች ሁሉ ዓይነተኛው ምክንያት የመለስ ዜናዊ አገዛዝ መሆኑ ማንም ሊጠራጠረው ባይችልም፥ በኢትዮጵያ የመንግሥት ለውጥ ለማምጣት የሚደረገው ትግል ገና ከመጻህ ደረጃ ከፍ ሊል አልቻለም በማለት ቁጭታቸውን የሚገልጹ የፖሊቲካ ተከታታዮች በርካታ ናቸው:: ለማነኛው ሀገር ሁልአቀፍ ችግርም ይሁን ልማት፥ ብልፅግናም ይሁን ድህነት፥ ሰላምም

ይሁን አለመረጋጋት የመጀመሪያው ተጠያቂ ያው በሥልጣን ላይ የሚገኘው ቡድን ነው:: ለዚህ መሠረታዊ ሀቅ ዝርዝር ትንታኔ የሚያሻው አይሆንም:: ሰላም፥ መረጋጋት፥ ብልፅግና፥ ልማት፥ ዕደገትና የወደፊት ርምጃ የሚከሰተው ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ሲሰፍን፥ የህግ የበላይነት ሲገኝና የሕዝብ ልዕልና ሲረጋገጥ ለመሆኑ ተደጋግሞ ተደጋግሞ የተነገረ ነው:: በአንፃሩ ደግሞ፥ በአምባገነንና በጸረ-ሕዝብ ጸረ-ሀገር ቡድኖች የምትመራ ሀገር፥ ክድህነት አርንቋና ከጦርነት አዙሪት ልትላቀቅ አትችልም፤ ለዚህ ዓይነተኛ ምሳሌ የምትሆነው ሀገራችን ኢትዮጵያ ለመሆኗ፥ ያለፈውን እንኳ ትተነው፥ ከዓለፉት ሠላሳ ዓመታት ወዲህ ያለውን ሁኔታ ብቻ መገምገሙ ይበቃል:: የፖለቲካ ስልጣን ሕዝብ በመረጠው ዴሞክራሲያዊ አገዛዝ እጅ እስካልሆነ ድረስ ችግሮችን ከስራቸው ነቅሎ ለማስወገድ ከቶም አይቻልም:: የቀስ በቀስ ለውጥ መርህም ራሱን በራሱ ጠልፎ በአፍጢሙ የሚደፋ መሆኑ አይቀሬ ነው:: ለዚህም ነው ሕዝብ ከአደናጋሪዎች ወጥምድ ተላቅቆ ይህን አገዛዝ በማስወገድ ወሳኝ ተልዕኮ ላይ ብቻ ማተኮር ያለበት::

የኢትዮጵያን ረሀብ አስመልክቶ በጣም እጅግ በጣም ሰፊና ጥልቅ ጽሁፎች ተጽፈዋል:: ኀልቆ መሳፍርት የሌላቸው የመፍትሄ ኃሳቦችና ዕቅዶች ተዘርዝረዋል:: በሚሊዮን ሳይሆን በቢሊዮን የሚገመት የውጭ ርዳታ ተለግሷል:: የዓለም ታላላቅ ዘፋኞችና የኪነጥበብ ሰዎች የዓለምን ኀብረተሰብ አዕምሮ ቀይረዋል:: አንጀት በልተዋል:: አስለቅሰዋል:: የኃይማኖት ተቋማትና ምዕመናን ፈጣሪያቸውን ተማጽነዋል:: የረሃብተኛውን አጽም ያየ የተመለከተ ሁሉ፡ አንጀቱ ተንሰፍስፏል:: የዓለም ህፃናት በአቅማቸው፥ ከምሳቸውና ከዕራታቸው ቀንሰው የርዳታ እጃቸውን ዘርግተዋል:: የዓለም መንግሥታት፥ ተቋማትና ድርጅቶች ሁሉ ተባብረዋል:: ሀገራችንም የተፈጥሮን ፀጋ አልተነፈገችም:: ይህ ሁሉ ሆኖ፥ ከሀያ ዓመታት በኋላ ዛሬም በኢትዮጵያ ሀገራችን በሚሊዮን የሚቆጠሩ ዜጎች በረሀብ ይረግፋሉ:: ያልቃሉ:: ዛሬም በርሀብ ምክንያት ዜጎች ከቤታቸው ከጓሯቸው ይሰደዳሉ:: ምፅዋዕት ይጠይቃሉ:: ሀዘኑ፥ ዋይታው፥ ዕሮሮው ሰቆቃው መከራና ስደቱ አሁንም መቆሚያ አልተገኘለትም:: ዛሬ ረሀብ ማለት ኢትዮጵያ ነች የሚል ሁለተኛ ስም ተሰጥቷናል:: ዓለም ታዝቦናል፥ ሰልችቶናል:: ፊቱንም አዞሮብናል::

"ከማነኛው በላይ የሚያስፈራው፥ የሚያሳፍረውና አንገት የሚያስደፋው፥ ምፅዋዕት በመለመን የሰው እጅ ዓይን አይን ማየት ነው" እንደሚባለው ሁሉ፥ ዛሬም ይህ ፍርሀትና ሃፍረት አለቀቀንም፡ ዕድሜ ለወያኔ!

ዘለዓለም፤ የውሀ መጥለቅለቅ፥ የመሬት መንቀጥቀጥ፥ የአየር እሳተ ገሞራነት፥ ዕድል ፋንታ የሆነባቸው እንደ ጃፓን ያሉ ሀገሮች፥ በርሀብ ሲያልቁ፥ ምፅዋዕት ሲጠይቁ፥ ርዳታ ሲለምኑ፤ አልታዩም አልተሰሙም:: ተፈጥሮ በብዙ መልኩ ቢበድላቸውም፤ ሸንጣቸውን ገትረው ቀበቷቸውን አጥብቀው ተፈጥሮን አቸነፉ እንጅ፥ ለረሀብ አልተሸነፉም:: ይህንን ብልኃት ያዩ እንደነ ከበደ ሚካኤል፥ እንደ ግርማቸው ተክለኃዋርያት የመሳሰሉ ደራሲያን የዛሬ አርባና አምሳ ዓመት ገደማ፤ እስቲ እኛም ከእነሱ እንማር

ብለው ጽፈው ነበር፡፡ ዛሬም የረሀብ ሰለባ የሆንነው ባየሩ በምድሩ ምክንያት ሳይሆን፤እርሶ አደሩ ሰነፍ ሆኖ ሳይሆን አገዛዙ የሚከተለው ፖለቲካና የእርሻ ፖሊሲ ወይም የመሬት ይዞታ በአጠቃላይ የተበላሸና ለኪሳራ የሚዳርግ በመሆኑ ነው፡፡ ኢትዮጵያን የጃፓኑ ይቅርና ከሌሎች አፍሪካ ሀገሮች ስናወዳድራት ቁልጭ ብሎ የሚታየው ሀቅ ይህ ነው፡፡ የኢትዮጵያ የወቅቱ ድርቅ ስሙ ወያኔ ኢሕአዴግ ነው፡፡

ስለዚህም በእኛ ዕምነት፥ ሀገራችንን፥ ከውርደት፥ ከረሃብና ድኅነት፥ ምዕዋዕትና ልመና፥ ለማላቀቅ ያለው ብቸኛ አማራጭ፥ ሕዝቡን የሚያሳትፍ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት መመሥረትና ተጠያቂነቱ ለሕዝብ የሆነ መንግሥት መሰየም ነው እንላለን፡፡ ይህ ደግሞ በምኞትና በመልካም ተስፋ የሚመጣ አይሆንም፡፡ ከመለስ ዜናዊ ጋርም ተደራድሮና ተሞዳምዶም የሚመጣም አይደለም፡፡እጅና ዕግርን አጣጥፎም የሚመጣ ለውጥ አይኖርም፡፡ የህይወት መሥዋዕት መክፈሉ ቢሆንም አስፈላጊ ነው፡፡ ሁሉም የድርሻውን ትንሽ ትንሽ መስዋዕት መክፈል ይጠበቅበታል፡፡ ይህን ለማድረግ፦

1ኛ ማነኛውም ለውጥ ፈላጊ ዜጋ ለለውጥ የሚያስፈልጉትን ጉዳዮች ሁሉ ማድረግ አለበት፡፡

2ኛ ተቃዋሚ ድርጅቶች የሚጠናከሩበትን ሁሉ ማከናወን ይጠበቅበታል፡፡

3ኛ የመለስ ዜናዊ ፕሮፓጋንዳ ሰለባ እንዳይሆን መጠንቀቅ ይኖርበታል፡፡
ከወያኔ የንንግድ ተቋማት ጋር ምንም ዓይነት ግንኙነት ሊያደርግ አይገባውም፡፡

4ኛ በዘርና በሃይማኖት ክፍፍል ወጥመድ እንዳይገባ እራሱን መከላከል ብቻ ሳይሆን፥ ይህንን መርዘኛ ሥርዓት፥ በመሆነው ዘዴ መዋጋት ግዴታው ነው፡፡

5ኛ ከወያኔ ኅልፈት በኋላ የኢትዮጵያ ሕዝብ አብሮ ተባብሮ መኖሩን መዘንጋት የለበትም፡፡

6ኛ የወያኔ ሥርዓት አባሪ ተባባሪ የሆኑትን የሀገር ጠላቶች ለይቶ ማወቅና ሰላዮቹን ከጉያው እየመነጠረ ማውጣት የወያኔን ዕድሜ እንደማሳጠር መሆኑን መገንዘብ አለበት፡፡

7ኛ ልጆቹንና ቤተሰቡን ከቻለም፤ አካባቢውን ከኤድስ በሽታ መካላከል፥ የነገውን ትውልድ ማትረፍ መሆኑን ለአንዳፍታም ቢሆን መርሳት የለበትም፡፡

8ኛ ለማይቀረው የሞትና የሽረት ትግል፥ ራሱን ማዘጋጀት ሀገሩን ከወያኔ መንጋጋ ለማላቀቅ ወሳኝነት እንዳለው ማወቅ አለበት፡፡

9ኛ ሀገሩን አሁን ካለችበት ማጥ ለማውጣት በግድ መሠረታዊ ለውጥ እንደሚያስፈልግ ማንም ሊነግረው አይገባም።

10ኛ እያንዳንዱ ዜጋ ንቁ ተሳትፎ ካላደረገ ሀገርን ማዳን አለመቻሉን አውቆ ብሔራዊ ግዴታን መወጣት ታሪካዊና ብሄራዊ ተልዕኮ መሆኑን ማንም ዜጋ ከኅሊናው ሊፍቀው አይገባውም።

ከረሀብና በሽታ፣ ከጭቆናና አፈና፣ከድህነትና ውርደት ልንላቀቅ የምንችለው ከመለስ ዜናዊ አገዛዝ ስንላቀቅና በነፃ ምርጫ የራሳችንን መንግስት ስንሰይም ብቻ ነው።